# በማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል
# የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ

## የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

(2016-2022 ዓ/ም)

መስከረም 2016 ዓ/ም

ወራቤ፣

## ይዘት ገጽ


መግቢያ ..... 3

ደረጃ አንድ፡- ተቋማዊ ዳሰሳ ..... 4

1.1 የቢሮው አጠቃላይ ገጽታ ..... 4

1.2 ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ እና የተገልጋይና የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና ..... 15

1.2.1 የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ ትንተና ..... 15

1.3 የቢሮው ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማዎችና ዕሴቶች ..... 21

1.3.1 ተልዕኮ ..... 21

1.3.2 ራዕይ ..... 21

1.3.3 እሴቶች ..... 21

1.3.4 ተቋማዊ ፍልስፍና ..... 21

ደረጃ ሁለት፡- ተቋማዊ ስትራቴጂን መወሰን ..... 22

2.1 የሴክተሩ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ዝርዝርና ዳሰሳ ..... 22

2.1.1 ተገልጋዮች /የአገልግሎት ተጠቃሚዎች/ ..... 22

2.1.2 ባለድርሻ አካላት ..... 22

2.2 የተቋም ስትራቴጂያዊ ትኩረት መስክና ስትራቴጂያዊ ውጤቶችን መለየት ..... 28

2.3 ስትራቴጂያዊ ዕይታዎች ..... 32

2.3.1 ተገልጋይ ..... 32

2.3.2 የፋይናንስ /በጀት/ ዕይታ ..... 32

2.3.3 የውስጥ አሰራር ዕይታ ..... 32

2.3.4 የመማማርና ዕድገት ዕይታ ..... 32

ደረጃ ሶስት፡- ስትራቴጂያዊ ግቦች ..... 33

ደረጃ አራት፡-ስትራቴጂያዊ ማፕ ማዘጋጀት ..... 39

ደረጃ አምስት፡-የአፈጻጸም መለኪያዎችን /Measures/ እና ዒላማዎችን /Targets/ ማዘጋጀት ..... 42

ደረጃ ስድስት፡-ስትራቴጂያዊ ዕርምጃዎች ..... **Error! Bookmark not defined.**

6.1 የስትራቴጂያዊ እርምጃዎችና ስትራቴጂያዊ ግቦች ትስስር ማሳያ **Error! Bookmark not defined.**

ደረጃ ሰባት፡- የአፈጻጸም መረጃ ሥርዓት መዘርጋት ..... **Error! Bookmark not defined.**

ደረጃ ስምንት፡- ውጤት ተኮር ዕቅድን በየደረጃው ለሚገኙ ፈፃሚዎች ማውረድ ..... **Error! Bookmark not defined.**

8.1 የሴክተሩን ውጤት ተኮር ዕቅድ ወደ ፈፃሚ አካል የማውረድ ምንነት....... Error! Bookmark not defined.

8.2 ስትራቴጂውን ወደ ፈፃሚ አካል የማውረጃ ዘዴና መርሃ ግብር.. Error! Bookmark not defined.

ደረጃ ዘጠኝ፡-የአፈፃፀም ክትትል ግምገማና ምዘና ........................................ Error! Bookmark not defined.

9.1 የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ .................... Error! Bookmark not defined.

9.1.1 ክትትል፡-.......................................................................... Error! Bookmark not defined.

9.1.2 ግምገማ ፡- .................................................................... Error! Bookmark not defined.

9.1.3 የክትትልና ግምገማ ስልት ..................................................... Error! Bookmark not defined.

9.1.4 የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሠንጠረዥ ............................ Error! Bookmark not defined.

9.1.5 የሴክተሩ የው.ተ.ስ ዕቅድ ግምገማ አደረጃጀትና ተግባራት... Error! Bookmark not defined.

## መግቢያ

የክልሉ መንግስት በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን ሀገራዊ ለውጥ ውጤታማ፣ ዘላቂና ተቋማዊ ለማድረግ እንዲሁም ከደረስንበት የዕድገት ደረጃ አንጻር የሚኖረውን ክልላዊ ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት የሚያስችል የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ፈትሾ ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ ታምኖበት ቀደም ሲል የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ የተሻሻለው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 199/2015 ሆኖ መጽደቁ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም ቢሮው ከክልሉ እስከ ቀበሌ ባሉ መንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈና የተደራጀ እንዲሆንና አገልግሎት አሰጣጡ ዘመናዊ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማስፈንና የሃብት ብክነትን መቀነስ ነው፡፡

በተጨማሪም በህብረተሰቡ ውስጥ ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂን በመዘርጋትና በማስፋፋት ህብረተሰባችን የግብርና፣ የገበያ፣ የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች መረጃዎችን በአቅራቢያው እንዲያገኙ በማድረግ በገጠርና በከተማው ህብረተሰብ መካከል ያለውን የዘመናዊ መረጃ ቴክኖሎጂ ክፍተት ማጥበብ ነው፡፡ በተጓዳኝም ቢሮዉ ፈጣን እድገት ለማረጋገጥ የግሉ ዘርፍ ቴክኖሎጂውን ለማስፋፋት የሚጫወተውን ሚና ግምት ውስጥ በማስገባት በሂደት የሚጎለብትበትንና የሚስፋፋበትን መንገድ ማጠናከር ነው፡፡

የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ የአስር ዓመት የመጀመሪያ መሪ የልማት ዕቅድ ከ2016-2022 ዓ.ም ባለው የ7 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን ውስጥ በየደረጃው ባሉ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ ዓላማ ተኮርና የወል ዳይሬክቶሬቶች የሚከናወን ሲሆን ሰነዱ አጠቃላይ የተቋሙን ዳሰሳ፣ የውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራን ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ዘጠኝ ድረስ ያለውን አካትቶ የያዘ ሲሆን የዕቅድ ሰነዱ አንድ ስትራቴጀያዊ የትኩረት መስኮችን፣ ስትራቴጂያዊ ግቦችን፣ መለኪያዎችን፣ ዒላማዎችን እና ስትራቴጂያዊ እርምጃዎችን፣ የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓትን የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

# ደረጃ አንድ

# ተቋማዊ ዳሰሳ

## 1.1 የቢሮው አጠቃላይ ገጽታ

ባለፉት ዓመታት በክልላችን የሰላም፣ የዲሞክራሲና የልማት ተግባሮች ለማከናወን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተነደፈው በብቃት ሊያስፈጸም የሚችል አቅም የተሟላ ሲሆን ባለመቻሉ ከክልል እስከ ቀበሌ በአጠቃላይ የመንግስት መዋቅር የሚታየውን የማስፈጸም አቅም ችግሮችን ለመቅረፍ የአቅም ግንባታ ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን የሚያስተባብርና በበላይነት የሚያስፈጽም ተቋማዊ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የክልሉን አስፈጻሚና ፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 36/1994 እንደገናም ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/95 የአቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ሆኖ ሲቋቋም የኢንፎርሚሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከ15 የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች እንደ አንድ አቅም ግንባታ ፕሮግራም ተቀርጾ ሲተገበር ቆይቷል፡፡

ዘርፉ ከ1996 ጀምሮ በቡድን ከዚያም በ1998 በመምሪያ ደረጃ እንዲሁም ከ 2000 ሃምሌ ጀምሮ በስራ ሂደት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ በመቀጠልም በክልሉ የአስፈጻሚ መ/ቤቶችን ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን እንደገና በወጣው አዋጅ ቁጥር 127/2002 መሰረት በአቅም ግንባታ ቢሮ ስር የኢኮቴ ልማት ኤጀንሲ በመሆን የተቋቋመ ሲሆን በመቀጠል በክልሉ የአስፈጻሚ መ/ቤቶችን አደረጃጀቶችና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰንና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 133/2003 መሰረት የክልሉ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ሆኖ ተጠሪነቱ ለር/መስተዳደሩ ሆኖ በዚሁ መሠረት ተቋቁሟል፡፡ በመቀጠልም በ2008 ዓ.ም ተጠሪነቱ ለክልሉ ፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በማድረግ በተሻሻለው የአስፈጻሚ ተቋማት ማቋቋምያ ደንብ ቁጥር ፻፴፮/2ሺ፰ እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ቀደም ሲል የቴክኖሎጂ ምርምርና ሽግግር ማዕከል ከተሰጠዉ ተልዕኮ በተጨማሪ የሳይንስና ተክኖሎጂ ተግባራት ታክለዉበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ በሚል ስያሜ በደንብ ቁጥር 152/2009 እንዲቋቋም ተደርጎ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተግባራትን ሲከውን ቆይቷል ፡፡

በመጨረሻም አሁን በሀገራችን ከመጣው ለውጥ ጋር ተያይዞ የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለአገልግሎት አሰጣጥ ምቹ ሆነው እንዲደራጁ በተቀመጠዉ አገራዊ አቅጣጫ መሰረት በክልሉ ምክር ቤት የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 180/2012 በአዲስ መልክ የተቋቋመዉ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ የሚጠበቅበትን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል እንዲሁም ከዚህ ቀደም የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ እና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ኢንስቲትዩት ኃላፊነቶችና ተግባራትን በአንድ ላይ በማዋሃድ በቢሮ ደረጃ እንዲደራጅ ሆኗል፡፡

ቀድሞ የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ፈርሶ በአዲስ መልክ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በመደራጀቱ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ እንዲደራጅ በክልሉ ምክር ቤት የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 199/2015 መሰረት ተደራጅቶ በመህበራዊ ክላስተር ወራቤ ማዕከል ስራ ጀምሯል፡፡

## 1.2 የክልሉ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ቢሮ የእትዕ-2 የአምስት ዓመት የዕቅድ ዘመን አፈጻጸም ግምገማ

**የትኩረት መስክ 1፡-**የመንግስት የኢኮቴ መሠረተ ልማት ዝርጋታ፣አገልግሎትና አስተዳደር

**ከትኩረት መስኩ የሚጠበቅ ውጤት፡-** በስፋትና በጥራት ያደገ በኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ የተደገፉ የመንግስት አገልግሎቶች፣

- **መረጃ ልውውጥና አስተዳደርን ለማሻሻል የመረጃ መረብ አውቶሜሽን ስራ የተገበረ የመንግስት ተቋማትን ብዛት ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
  - የዋይድ ኤሪያ መረጃ መረብ (WAN) በዕቅድ ዘመኑ የተዘረጋው በአራት ተቋማት ብቻ ቢሆንም ውጤታማ እየሆነ ያለ ሲሆን የተደራሽነት ችግር የሚታይበት ነው፡፡ የአካባቢያዊ መረጃ መረብ (LAN) ዝርጋታ ስንመለከት በየአከባቢው ተደራሽ ለማድረግ ጥረት የተደረገ ሲሆን በአብዛኛው ተቋማት በስታንዳርድ መሰረት ያልተሰራ በመሆኑ የእኛን ተቋም ጨምሮ ከፍተኛ የሆነ የጥራት ችግር ይታያል፡፡
- **የአሰራር ስርዓት ሂደታቸውን ለማቀላጠፍ የአፕልኬሽን ሶፍትዌር አውቶሜሽን ስራ የተገበረ የመንግስት ተቋማትን ብዛት ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
  - ለኢንፎርሜሽን ስርጭትና ለገጽታ ግንባታ የሚያገለግሉ ሰባ አምስት የድረ ገጽ ልማት ለማከናወን ታቅዶ ሰባ አንድ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 94.6 በመቶ ነው፡፡

- የድህረገጽ ልማት ስራችን በአንጻራዊነት ጥሩ ቢሆንም ቀጣይነትና ጥራት ያለው አገልግሎት ከመስጠት አኳያ የውጤታማነት ችግር አለበት፡፡ የድህረገጽ ልማት ስራ ስትራቴጅክ ያለመሆን ችግር /ችግር ፈቺ የድህረገጽ ልማት ስልጠና ያለመስጠት እና የለሙ ድህርገጾችም ቢሆኑ ወቅታዊ የማይደረጉ በመሆናቸው የተቋማትን ታአማኝነት እየቀነሰ መሆኑ፣ በጥቅሉ ውጤታማነት ችግር ያለበት ነው፡፡

- የክልሉን የመረጃ ስርጭት ከፍተኛ ለማድረግና ለመረጃ ልውውጥ እንዲሁም አሰራራቸውን ለማስተዋወቅ አንድ ማዕከላዊ ፖርታል ለማልማት ታቅዶ ስራው ሙሉ ለሙሉ ተከናውኗል፡፡
  - የማዕከላዊ ፖርታል ልማት ስራ ይጀመራል ይቆማል በውስጥ አቅም ለማልማት አድቫንስ ስልጠና ቢሰጥም በባለሙያዎች መልቀቅ፣ የክህሎት ክፍተት እና የክትትል ችግር ምክንያት ውጤታማ ሳይሆን ቀርቷል፡፡

- አስፈላጊ መሆናቸው የታመነባቸውአስር ሶፍትዌሮችለመንግስት መ/ቤቶች ለማልማት ታቅዶ አስር ሶፍትዌሮችን ማልማት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም መቶ በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም አስራ ሶስት ሶፍትዌሮችን ወደ ክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ የማላመድ ስራ ለማከናወን ታቅዶ አስራ አንድ ሶፍትዌሮችን ማላመድ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 85 በመቶ ነው፡፡
  - የሶፍትዌርና ሲስተም ልማት ስራ በዕቅድ ዘመኑ ከሦስት ያልበለጠና ውጤታማ ያልሆነ ሲሆን ሌሎች ተቋማት በዩንቨርስቲዎች እና በአማካሪ ያስለሙት ሶፍዌርና ሲስተም ውጤታማ እንደሆነ መገምገም ተችሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሚነሳው የክህሎት ክፍተት፣ ማበረታቻና ጥቅማጥቅም አለመኖር፣ ፍልሰትና ተከተታይ ፕሮጀክት ቤዝ ስልጠናዎች አለመኖራቸው፤

- **የተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሳለጥ የተሰራጩ ዘመናዊና ወቅታዊ የኢኮቴ መሳርያዎችን ቁጥር ለመጨመርበተጣለ ግብ፤**

- በጥናት ላይ በተሠረተ ፍላጎት መለያ መንገድ ለአንድ መቶ ሀያ ሶስት ተቋማት የኢኮቴ መሳርያዎች ለማቅረብ ታቅዶ ለሀያ ተቋማት ማቅረብ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 16 በመቶ ነው፡፡
  - ይህ ተግባር ቀደም ሲል በፒስካፕ ፕሮጀክት የኢኮቴ መሳሪያዎችን እየገዛ ሲያሰራጭ ቆይቶ ፕሮጀክቱ ሲቆም በመንግስት በጀት እየገዙ ማሰራጨት

ባለመቻሉ ማሳካት አልተቻለም፡፡ ግብን ለማሳካት የኢኮቴ መሳሪያዎች ቁጥር ይልና መለኪያው ተቋማት ቁጥር ነው ይህ ተገቢም አይደለም፡፡

- **ወቅታዊ ደህንነቱ የተጠበቀና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚችል ክልላዊ የዳታ ማዕከል ተጠቅመው የመረጃ ልውውጥና አስተዳደር ስርዓታቸውን ያሻሻሉ ተቋማት ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
  - የወረዳኔት መሰረተ ልማት ተጠቃሚ የሆኑ ተቋማትን ቁጥር አርባ አምስት ለማድረስ ታቅዶ በአርባ ሁለት ተቋማት ላይ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 93 በመቶ ነው፡፡
  - ወረዳኔት መሰረተ-ልማት የሚጠቀሙ ተቋማትን ለማሰፋት የተኬደበት ረቀት ጥሩ የሚያበረታታ ሲሆን አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታን የሚለካ መለኪያ ያልተቀመጠለት በመሆኑ በግቡ መሰረት የመረጃ ስርዓታቸውን ያሻሻሉ ተቋማትን መገምገም አልተቻለም፡፡ ሆኖም የታችኛው መዋቅሮች ዞኖች በተለይ የወረዳና ከተማ አስተዳደር የወረዳኔት ክፊያ ባለቤትናት ስሜት ማጣት እና አለመክፈል የመረጃ ልውውጥና አስተዳደር ስርዓታቸውን እንዳይሻሻል አድርጎታል፡፡ ሲጠቃለል የባለቤትነትና የክፊያ አከፋፈል ስርኣት ስልት ቢታሰብ፣
- **የስልጠናና የጥገና ማዕከላት ለማቋቋም በተጣለ ግብ፤**
- በየደረጃው አስራ ዘጠኝ የስልጠና ማዕከላት ለማቋቋም ታቅዶ አስራ አራት ተቋቁሟል፡፡ አፈጻጸሙም 74 በመቶ ነው፡፡
  - ስልጠና ማዕከል ለማቋቋም የተኬደበት ረቀት አበረታች ሆኖ ግቡ በራሱ ማቋቋም ብቻ በመሆኑ ማዕከሉ ከተቋቋመ በኃላ የሚሰጠውን አገልግሎት እሴቶች በአግባቡ የሚለካ መለኪያ ያለመኖር፣ ስልጠና ማዕከል ደረጃ ስታንዳርድ አለመኖር እንዲሁም ለማቋቋም በቂ ሀብት ያለመመደብ ችግር ጭምር ታይቷል፡፡
- በየደረጃው አስራ ዘጠኝ የጥገና ማዕከላት ለማቋቋም ታቅዶ አምስት ለማቋቋም ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 26 በመቶ ነው፡፡
  - ጥገና ማዕከል ለማቋቋም ከዕቅድ አኳያ ዝቅተኛ ሲሆን ግቡ በራሱ ማቋቋም ብቻ በመሆኑ ማዕከሉ ከተቋቋመ በኃላ የሚሰጠውን አገልግሎት እሴቶች በአግባቡ የሚለካ መለኪያ ያለመኖር፣ ማዕከል ደረጃ ስታንዳርድ አለመኖር እንዲሁም ለማቋቋም በቂ ሀብት ያለመመደብ ችግር ጭምር ታይቷል፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ግቡን

ማሳካት አልተቻለም ስለሆነም አፈጻጸም ስልት በአዲስ መልክ ማስቀመጥ ይጠይቃል፡፡

- **የአገልግሎት አሰጣጥን ደህንነት፣ ቀጣይነት፣ ቀልጣፋነትና ውጤታማነት በማሣደግ የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ለማሻሻል በተጣለ ግብ፤**
- ሀምሳ ሁለት ዌብ ሳይቶችንና ሲስተሞች ደህነታቸው ተጠብቆ ሆስት ለማድረግ ታቅዶ ሀያ አራት ዌብሳይቶችና ሲስተሞች ሆስት ተደርገዋል፡፡ አፈጻጸሙም 46 በመቶ ነው፡፡
    - የሆስቲንግ ስራ በቅርቡ በትግል ማስጀመር የተቻለ ሲሆን የሆስቲንግ ስራ ማጠናከር የሚያስፈልግ ሲሆን የሆስቲንግ አገልግሎት ስታንዳርድ ማንዋል ያለመኖር፣ ዌብሳይትንና ሲሰተምን በቁጥር ለይቶ ያለመለካት፣ በመሆኑም የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መሻሻሉን ያለመለካት ችግር ማረም ያስፈልጋል፡፡
- አራት የክልል ተቋማትን የባክአፐ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ ሶስት ተቋማትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 75 በመቶ ነው፡፡
    - አጠናክሮ ማስቀጠል
- ሶስት የመንግስት ተቋማትን በአነስተኛ ወጭና አስተማማኝ የክላውድ አገልግሎት የግንባታ፣ የአስተዳደር፣ የድህንነት ጉዳይ ሳያስቡ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታቅዶ ለሁለት ተቋማት ማሳካት ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 67 በመቶ ነው፡፡
    - በቀጣይ ማጠናከርና የክላውድ አገልግሎት ቦልድሊ በግብ ደረጃ ማሰብ ይጠይቃል፣
- **የተቋማትን የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን የሚያሳልጡ ዘመናዊ ኢኮቴ መሰረተ ልማቶች ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በተጣለ ግብ፤**
    - ለስምንት ተቋማት የተጠናከረ አውቶሜትድ የሆነ የአሰራር ስርዓት፣ አገልግሎትና የመረጃ አያያዝ እንዲዘረጋላቸው ታቅዶ በአስራ ሶስት ተቋማት ተተግብሯል፡፡ አፈጻጸሙም ሙሉ በሙሉ ነው፡፡
- **የለሙ ሲስተሞችና ሶፍተዌሮችን ማስተዳደር የሚያስችል ዳታ ማዕከል አቅም ለመገንባት በተጣለ ግብ፤**
- የለሙ ሲስተሞችና ሶፍተዌሮችን ለማስተዳደር የሚያስችል የተገነባ የዳታ ማዕከል አቅም ሰባ አምስት በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ስልሳ ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡
    - የዳታ ማዕከል አቅም ለመገንባት የተኬደበት ረቀት ጥሩ ሲሆን የማዕከሉ ግንባታ ከምን አንጻር 67.5 ፐርሰንት እንደደረሰ ግልጽ ያለመሆን ችግር በሌላ አገላለጽ የዳታ ማዕከል አቅም ግንባታ ከስታንዳርድ ማንዋል አንጻር አለመሆን ችግር

ማረም ያስፈልጋል። በሌላ በኩል የማዕከሉ አቅም መገንባት የመጨረሻ ውጤት ስላልሆነ ከተገነባ በኃላ የሚሰጠውን አገልግሎት በዝርዝር መለኪያ ማየት ያስፈልጋል።

- **ክልላዊ የመንግስት ዳታና ቪዲዮ አገልግሎት ተጠቃሚ ተቋማትን ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- ሰላሳ ሰባት ተቋማት የቪዲዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ ሰላሳ አንድ ተቋማትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። አፈጻጸሙም 84 በመቶ ነው።
    - የቪዲዮ ኮንፍረንስ አገልግሎት ተጠቃሚ ተቋማት ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ የሚያበረታታ ሲሆን ቪዲዮ ኮንፍረንስ በመጠቀማችን ይባክን የነበረውን የመንግስት ሀብት በመለኪያነት ያለመገለጽ፣
- **በተቋማት መሰረተ ልማት እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተዘረጉ የስኩልኔት መሰረተ ልማቶች ቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ተገቢውን አገልግሎት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ በተጣለ ግብ፤**
- ለአምስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ለአምስት መቶ አርባ ሁለት ማድረግ ተችሏል። አፈጻጸሙም 92 በመቶ ነው።
    - የስኩልኔት መሰረተ ልማቶች ቴክኒክ ድጋፍ በተገቢው መስጠት መቻሉ ተገምግሟል። ስለሆነም ትምህርት ቤቶች የስኩልኔት አገልግሎት መስጠት አለመስጠቱ የተቋማችን ተልዕኮ ስላልሆነ በግብ ደረጃም መገለጹ ተገቢ አለመሆኑን መግባባት ተችሏል።
- ግቡንን በደንብ ማየትና በመለኪያ ማሳየት ያስፈልጋል ድጋፍና ክትትል ብቻውን ግብ ሊሆን አይችልም
- **ለመንግስት የኢኮቴ የመረጃ ስርዓት ልማትና አስተዳደር የለሙ፣የተዘረጉና የቀረቡ መሠረተ ልማቶችን አስተማማኝነትና ቀጣይነት ማረጋገጥ ለማስቻል ጥገናና ማሻሻያዎችን ለማድረግ በተጣለ ግብ፤**
- ለሀምሳ ሺህ የኢኮቴ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለሰላሳ ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ተከናውኗል። አፈጻጸሙም 61 በመቶ ነው።
    - የኢኮቴ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት የተሰጠበት ሁኔታ የሚያበረታታ ሲሆን በጥገና የዳነውን ገንዛብ በመለኪያነት ቢካተት፣ ጥገናዎች በስታንዳርድ/ በማንዋሉ መሰረት ይሁን አይሁን ግልጽ ቢሆን /ከባድ፣ ቀላልና መካካለኛ/

- **ክልላዊ የዕድሳት ማዕከልን በማጠናከር ታድሰው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የኢኮቴ መሳሪያዎች ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- የዕድሳት ማዕከሉን በቁሳቁስ ሰማኒያ በመቶ ለማሟላት ታቅዶ ሰባ በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡
  - ማዕከል አቅም ለመገንባት የተኬደበት ረቀት ጥሩ ሲሆን የማዕከሉ ግንባታ ከምን አንጻር 70 ፐርሰንት እንደደረሰ ግልጽ ያለመሆን ችግር በሌላ አገላለጽ ማዕከል ከስታንዳርድ ማንዋል አንጻር አለመሆን ችግር ማረም ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የማዕከሉ መቋቋም የመጨረሻ ውጤት ስላልሆነ ከተቋቋመ በኃላ የሚሰጠውን አገልግሎት በዝርዝር መለኪያ ማየት ያስፈልጋል፡፡ ግቡን በአግባቡ የሚለካ መለኪያ ያለመኖር ችግር፣
- ለዳታ ማዕክ የተሰጠው አስተያየት ለጥገና ማዕከሉ ይሆናል
- ታድሰውና ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ያልቻሉትን ከሚኒስቴር መ/ቤት ጋር በመተባበር ስምንት መቶ ኪ.ግ. ቁሳቁሶች ለማስወገድ ታቅዶ ማከናወን አልተቻለም፡፡
- የትኩርት መስክ አንድ ላይ የተቀመጠውን ስትራቴክ ውጤት ከማስመዝገብ አኳያ ይህን ትኩረት መስክ ለማሳካት የተቀመጡ ግቦች ጥቂቶቹ አበረታች ቢሆኑም በአብዛኛው ግቦች በአንድም በሌላ ምክንያቶች አፈጻጸማቸው ዝቅተኛና ግቦቹን በአግባቡ የሚለኩ መለኪያዎች ጭምር አለመኖር የተገመገመ ሲሆን በቀጣይ ትኩረት መስኩን፣ ግቦችንና መለኪያዎችን በጥልቀት በማየት በአዲስ መልክ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡

**የትኩረት መስክ 2፡- የማህበረሰብን የኢኮቴ አገልግሎት ተጠቃሚነት፣ ክህሎትና ስርጸት ማሳደግ**

**የሚጠበቅ ውጤት፡-** የኢኮቴ ዕድሎችን በአግባቡ ተገንዝቦና በብቃት አማራጮቹንተጠቅሞ በየተሰማራበት ተልዕኮ ተጨባጭ እሴት መጨመር የቻለ ማህበረሰብ መፍጠር

- **ለማህበረሰቡ የኢኮቴ ግንዛቤ፣ ክህሎትና አገልግሎት በተገቢው መስጠት የሚችሉ የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላትን ማጠናከርና ተደራሽ ለማድረግ በተጣለ ግብ፤**
- አርባ አምስት የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላትን ለመቋቋም ታቅዶ ሰላሳ ሰባት ማከናወን ማቋቋመወም ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 82 በመቶ ነው፡፡
  - ማህበረሰብ መረጃ ማዕከል ከተደራሽነት አኳያ ጥሩ የተሰራ ሲሆን ማዕከሎቹ አገልግሎት ከመስጠት አንጻር በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚለካ መለኪያ አለመኖሩ፣ የታችኛው መዋቅሮች ማዕከል እንዲቋቋም በቂ ፍላጎት አለመኖር፣

ባለቤትነት ችግር፣ የዕቃዎች አረካከብ ችግር/ ስምምነት ውል አለመኖር/፣ ሌተስት እቃዎች /በርካታ ማቴሪሎችን መግዛት እየቻልን/ በከፍተኛ ዋጋ እየተገዛ ሪሞት አከባቢ መሄዱ ስለሆነም ሌላ አፈጻጸምና ግብ ስትራቴጂ ካልታሰበ በስተቀር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

- ሀያ አራት የማህበረሰብ መረጃ ማዕከላትን ደረጃቸውን ለማሻሻል ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡
  - ማዕከላት ደረጃው መሻሻሉ አበረታች ሆኖ ከተሸሻሉ በኃላ እየሰጡ ያሉትን አገልግሎት ሁኔታ ሚለካ መለኪያ አለመኖር፣
- **የኢኮቴ ውጤቶችን ተጠቅመው ተልዕኳቸውን በተሻለ ማሳካት የቻሉ መንግስት ሠራተኞችን ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- ለአስራ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና አንድ የመንግስት ሰራተኞች የኢኮቴ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለአስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ ሶስት ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 63 በመቶ ነው፡፡
  - ስልጠናውን የወሰዱ ሰልጣኞች ቁጥር ከማሳካት አንጻር ጥሩ ሆኖ ተልኳቸውን ማሳካት የቻሉ ሰራተኞችን የሚለካ መለኪያ ያለመኖር፣ ስልጠናውን ተደራሽ ለማድረግ የአተገባባር ስልት ቢታሰብ፣
- **የማህበረሰቡን ቋንቋ፣ ባህል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅሙን ማሳደግ የሚስችሉ የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎችን ተደራሽነት ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- አምስት የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎችን በክልሉ ለማቋቋም ታቅዶ ሁለት ማቋቋም ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 40 በመቶ ነው፡፡
  - በዕቅድ ዘመኑ የተቋቋሙት ጣቢያዎች ጥሩ ሆኖ በፌደራል መንግስት ድጋፍ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ እስካሁን ድረስ የክልል መንግስት በጀት ይዞ ተቋቋመ ጣቢያ የለም፣ ከማቋቋም ባለፈ የጣቢያዎቹ አገልግሎት ሁኔታን እና ያሉበትን ደረጃ የሚለካ መለኪያ አለመኖር ስለሆነም በቀጣይ ቢታሰብበት…

የትኩርት መስክ ሁለት ላይ የተቀመጠውን ስትራቴክ ውጤት የኢኮቴ ዕድሎችን በአግባቡ ተገንዝቦና በብቃት አማራጮቹን ተጠቅሞ በየተሰማራበት ተልዕኮ ተጨባጭ እሴት መጨመር የቻለ ማህበረሰብ መፍጠር ከሚለው አኳያ አኳያ ይህን ትኩረት መስክ ለማሳካት የተቀመጡ ግቦች ግቦች በአንድም በሌላ ምክንያቶች አፈጻጸማቸው ዝቅተኛና ግቦቹን በአግባቡ የሚለኩ

መለኪያዎች ጭምር ውስንነት ያለበት በቀጣይ ትኩረት መስኩን፣ ግቦችንና መለኪያዎችን በጥልቀት በማየት በአዲስ መልክ ማቀድ ያስፈልጋል።

**የትኩረት መስክ 3፡- የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስታንዳርዶች፣ ህጋዊ ሥርዓትንና ደህንነትን ማረጋገጥ**

**የሚጠበቅ ውጤት፡** የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ አገልግሎቶችና አሰራሮች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማስቻል፣

- **የብቃት ማረጋገጫና ፍቃድ ያገኘ የግል የኢኮቴ ኢንተርፕራይዞችን ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- ለ700 የግል ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ ለሶስት መቶ ሰባ አምስት መስጠት ተችሏል። አፈጻጸሙም 54 በመቶ ነው።
    - ህጋዊ ማዕቀፍ ተከትለው በንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ የድርሻቸውን እንዲወጡ ብቃትና ፍቃድ ያገኙ የኢኮቴ ኢንተርፕራይዝ ከዕቅድ አኳያ ጅምሩ ጥሩ ቢሆንም በክልላችን በዘርፉ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር አንጻር ውስን ቢሆንም በሌላ በኩል ማረጋገጫ ከመስጠት ባለፈ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት በምንደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚለካ መለኪያ በቀጣይ ይታሰብ፣
- ክትትል ከተደረገ በኃላ ምን ተደረገ ምን ማሻሻያ ተደረገ የመግለጽ ጉድለት አለበት፣
- **የግሉ የኢኮቴ ዘርፍ ድርጅቶች ለሚሰጡት አገልግሎት/ ምርት የሚገባቸውን ሀገር አቀፍ ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ማሟላታቸው ክትትል የተደረገላቸው ድርጅቶችን ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- በሰማንያ የግል ድርጅቶች ላይ የክትትል ስራ ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ተከናውኗል።
    - ጥሩ መጠናከር የሚገባው ነው፣
- ክትትል ከተደረገ በኃላ ምን ተደረገ ምን ማሻሻያ ተደረገ የመግለጽ ጉድለት አለበት፣
- **ወቅታዊ ስታንዳርድ ስፔስፊኬሽን የተዘጋጀላቸውን በክልሉ የሚለሙ/የሚቀርቡ የሶፍትዌር ልማቶች፣ የኔትወርክ ዝርጋታዎችና የኢኮቴ መሳያርያዎች ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- ለየኢኮቴ ምርትና አገልግሎቶች ስታንዳርድ ስፔስፊኬሽኖች 216 ለማዘጋጀት ታቅዶ ለአምስት ማከናወን ተችሏል። አፈጻጸሙም 2.3 % በመቶ ነው።

- ለየኢኮቴ ምርትና አገልግሎቶች ስታንዳርድ ስፔስፊኬሽኖች ለማዘጋጀት ጅምሩ ጥሩ ሆኖ ዕቅዱ ላይ የተቀመጠው ቁጥር የተሳሳተና ከስራው አንጻር የተጋነነ መሆኑ፣ በርካታ ምርቶች ስታንዳርድ ስፔክ መዘጋጀት ሲገባው ለአምስት ምርቶች ብቻ ከአቅም በታች የተሰራ መሆኑ፣

**የትኩረት መስክ 4፡-** የግሉን የኢኮቴ ዘርፍ ልማትን ማጠናከር፣ተወዳዳሪነቱንና ጥራቱን ማሳደግ

**የሚጠበቅ ውጤት፡** በቂና ደረጃጀውን የጠበቁ የኢኮቴ አገልግሎቶች፣ምረቶችና ውጤቶች በገበያ እንዲቀርብ ማሰቻል፡፡

- **ውጤታማ የግል ኢኮቴ ዘርፍ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- *ሀያ* የግል ኢኮቴ ዘርፍ ኢንተርፕራይዞች በማደራጀት ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዶ አስራ ስምንቱን ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 90 በመቶ ነው፡፡
  - ኢንተርፕራዞችን ቁጥር ማሳደግ የተሸለ ሲሆን የአሰራርና የአደረጃጀት ችግር በመኖሩ የሚደራጁት ኢንተርፕራይዞች ከሃዋሳ ከተማ ብቻ መሆኑ /ተደራሽነት ችግር/፣ የማደራጀት ስልጣን የሌላ አካል መሆኑ፣ ውጤታማነታቸውን የሚለካ መለኪያ አለመኖር፣
- **በክልል ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች ጋር የዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪ ትስስር ለማጠናከር በተጣለ ግብ፤**
- ከአስር ዩኒቨርስቲዎች ጋር የመግባቢያ ሰነድ ለመፈራረም ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ተከናውኗል፡፡
  - ይበል የሚያስብል ነው፣
- ☞ ሶስት መቶ አስራ አራት ተማሪዎች በኢንዱስትሪው ተገቢውን ልምምድ እንዲያደርጉ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡
  - የተግባር ላይ ልምምድ የሚያደርጉ ተማሪዎች አበረታች ሲሆን ከልምምዱ በኃላ ምን ያህሎቹ በተሸለ ደረጃ በቅተው መውጣታቸውን የሚለካ መለኪያ ቢኖር፣
  - ልምምድ ላይ የሚመጡ ተማሪዎችን በቼክ ሊስት በማስደገፍ ጥናት ማድረግ
- ☞ በክልሉ ሰባት ዩኒቨርስቲዎች ድጋፍ በማድረግ ኢንኩቤሽን ማዕከላትን ለማቋቋም ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

- ✍ በዩንቨርስቲዎች የተቋቋመው ኢንኩቤሽን ማዕከላት ጥሩ ሆኖ እንዲቋቋም የደረግነውን ድጋፍ የሚለካ መለኪያ አለመኖር፣ ማቋቋም የእኛ ኃላፊነት ባይሆንም የማዕከሉ የአገልግሎት ሁኔታ ያለበትን ደረጃ የሚለካ መለኪያ አለመኖር፣
- ☞ **የክህሎትና የግንዛቤ ስልጠናዎችን ያገኙ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- ☞ ለሁለት መቶ አርባ የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የክህሎትና የግንዛቤ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡
  - ✍ የክህሎትና የግንዛቤ ስልጠና አፈጻጸም የተሸለ ነው
- ☞ **በግብዓት የተጠናከሩ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- ☞ ሀያ ኢንተርፕራይዞችን በግብዓት ለማጠናከር ታቅዶ ለአስራ ስምንት ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 90 በመቶ ነው፡፡
  - ✍ በግብዓት የተጠናከሩ ኢንተርፕራይዞች አፈጻጸም ጥሩ ሲሆን የተቋቋሙት ማህበራ በቁጥር ደረጃ የተቀመጠውን ቁጥር 90 % የሚጠቅስ ቢሆንም የማህበራን ደረጃ ስለማይገልጽ ቢስተካከል
- ☞ **ለተደራጁ ኢኩቤቲዎች የተፈጠረ የገበያ ትስስር ለማሳደግ በተጣለ ግብ፤**
- ☞ ሰላሳ አምስት የገበያ ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ ሀያ ዘጠን መፍጠር ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 83 በመቶ ነው፡፡ የገበያ ትስስሩ ተጨማሪ ሀብት መፍጠር የሚል መለኪያ ቢኖረው፡፡
  - ✍ ግቡ ገበያ ትስስር ሆኖ ሲያበቃ መለኪያው የገበያ ትስስር በዙር/በቁጥር መሆኑ ግቡ መሳካቱን መለካት ያስቸግራል፣ የሚመረቁ ኢንተርፕራይዞችን ለመለየትም መለኪያው አስቸጋሪ ነው፡፡
- ☞ **በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤታማና ተወዳዳሪ የሆኑ የተመረቁ /ራሳቸውን የቻሉ/ኢንተርፕራይዞች ለመፍጠር በተጣለ ግብ፤**
- ☞ አስር የግል የኢኮቴ ኢንተርፕራይዞችን ራሳቸውን ችለው እንዲመረቁ ለማድረግ ታቅዶ ሶስት ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 30 በመቶ ነው፡፡
  - ✍ ራሳቸውን ችለው ያስመረቅናቸው ኢንተርፕራይዞች አፈጻጸም ዝቅተኛ ስለሆነ በጥቅሉ የትኩረት መስኩና የሚጠበቀው ውጤት እየተሳካ ስላልሆነ አሰራር፣ የአደራጃጀትና የአፈጻጸም ስልት በአዲስ መልክ ማሰብ ይጠይቃል፡፡

☞ **ክልላዊ የኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ኮንፍረንስ በማዘጋጀት የቢሮውን ተግባራትና ውጤቶችን ማስተዋወቅና ሀገር አቀፍ የኢኮቴ ሳምንት ለማክበር በተጣለ ግብ፤**

- ሁለት ጊዜ ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ኮንፍረንስ ለማዘጋጀት ታቅዶ አንድ ጊዜ ማከናወን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 50 በመቶ ነው፡፡

✍ ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ኮንፍረንስ ማዘጋጀት የሚለው 50 ፐርሰንት ጥሩ ሆኖ ተጨማሪ ግቡን የሚለኩ ሀገር አቀፍ የኢኮቴ ሳምንት መለኪያ አለመኖር፣ በመዘጋጀቱና በመከበሩ የተገኙ ለውጦችን የሚለካ አለመሆኑ፣ ዘንድሮ ኤግዚቢሽን፣ ባዛርና ኮንፍረንስ በኮሮና ቫይረስ ምክንያት አለመከበሩ፣

ጠንካራ ጎን

- ዕቅድ አዘጋጅቶ ለመተግበር ጥረት መደረጉ፣
- የዩንቨርስቲ ኢንዱስትሪ ትስስር በመፍጠር ቅንጅታዊ አሰራር ለመፍጠር ጅምር ስራዎች መኖራቸው፣
- የሆስቲንግና ዳታ ባክአፕ ስራዎች በጥረት መጀመር መቻሉ፣

ደካማ ጎን

- የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅት ማንዋልን ተክትሎ ከማዘጋጀት አኳያ ውስንነት ያለበት መሆኑ፣/ግቦች ከ15 በበላይ የመሆን ችግር፣
- ሪፖርት ከዕቅድ ጋር ያለመናበብ ችግር፣
- ግቦችን በአግባቡ የሚለካ የመለኪያ ውስንነት፣
- ስራ ክፍሎች ዕቅዳቸውን ከተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ ጋር በትኩረት ያለማናበብ ችግር፣

## 1.3 ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ እና የተገልጋይና የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና

### 1.3.1 የውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታ ትንተና

በዚህ ደረጃ የሴክተሩ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች ማለትም የጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚና ስጋት ትንተናን አጉልቶ የሚያሳይ ሆኖ በዚህ ትንተና ተልዕኮን ከማሳካት አንጻር የሴክተሩን የሥራ አካባቢ በውጫዊና ውስጣዊ ዝርዝር ሁኔታዎች ተመስርቶ የአዎንታዊ (አስቻይ) እና አሉታዊ (ፈታኝ) ተጽዕኖ ትንተና የሚቀርብበት ነው፡፡ ከትንተናው የሚገኘው ውጤትም ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫን ለማመላከት እንደ አንድ መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

በዚሁ መሠረት በሴክተሩ የተካተቱት ጥንካሬዎችና ድክመቶች ከአሰራር ስርዓት አደረጃጀት፣ ከአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከሰው ሃይል፣ ከአመራር ብቃት፣ ከስትራቴጂ፣ ከፋሲሊቲዎች፣ ከተቋማዊ ባህልና ከፋይናንስ አጠቃቀም አንጻር የሚዳሰስ ሲሆን መልካም አጋጣሚዎችና ሥጋቶች ደግሞ ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ቴክኖሎጂያዊና አካበቢያዊ ጉደዮች አንጻር በመዳሰስ ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## ሀ. የውስጣዊ ሁኔታ ትንተና

| | | አስቻይ ሁኔታዎች | ፈታኝ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የጥንካሬና ድክመት ማሳያ ዋና ጉዳዮች | ጥንካሬ | ድክመት |
| 1 | የአሰራር ስርዓት አደረጃጀት | ➢ ተቋማዊ የሪፎረም ስራዎች ጥናታዊ ስራዎች መጀመራቸው<br>➢ ሴክተሩ ራሱን ችሎ በቢሮ ደረጃ እንዲደራጅ ተደርጎ በሁለት ዘርፎች፣ በአስራ ሶስት ዳይሬክቶሬቶችና በአራት ሥራ ክፍሎች መደራጀቱ፡፡<br>➢ በክልሉ የሳንይስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ካልላዊ ምክክር ጉባዔ ተቋቁሞ ወደ ስራ ለማስገባት ጥረት እየተደረገ መነሆኑ<br>➢ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ተዘጋጅቶ ለመከለስ ዝግጅት ላይ መሆኑ፣<br>➢ የቢሮዉን የማቋቋሚያና የአደረጃጀት ደንብ እንዲሁም አበይት ተግባራት የሚያሳልጡ የተወሰኑ የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው መተግበር መጀመራቸው፣<br>➢ የተቋሙን አሰራር ለማዘመንና በሲስተም የታገዘ ለማድረግ የሚያስችሉ ሲስተሞች ልማት ስራ መጀመራቸውና በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተግባራዊነት ለማስገባት የሚያስችል ሁኔታ ላይ መሆናቸው<br>➢ ቴክኖሎጂን በመጠቀም መረጃንና ሪፖርቶችን የመለዋወጥ ስራዎች ጅምሮች መኖራቸው፣<br>➢ ቢሮው ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚስችለ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ በመፈራረም ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፣ | ➢ የታቀዱ ግቦችን በቢ.ኤስ.ሲ፤ በዜጎች ቻርተርና በካይዘን አሰራር ስልት በሚገባ አስተሳስሮ በየጊዜው ተግባራትን ቆጥሮ የመስጠትና ቆጥሮ ከመቀበል አንፃር ዉስንነት መኖሩ፣<br>➢ በየደረጃው የሚዘጋጁ ተቋማዊ ዕቅዶችና ሪፖርቶች ውስንነት መኖሩ፣<br>➢ በተገቢው ስትራቴጂያዊ ግቦችን የሚለኩ መለኪያዎች አለመጠቀም፤<br>➢ ተከታታይነት ያለው የክትትል፣ የግምገማ፣ ሪፖርቲንግና ግብረ-መልስ ስርዓቱ በሚፈለገዉ ልክ ጠንካራ አለመሆኑ፣<br>➢ የመረጃ አሰባሰብ፣ አያያዝና አጠቃቀም ድክመት መኖሩ፣<br>➢ እንደ ቴክኖሎጂ ተቋምነቱ የውስጥ አሰራሮች በሲስተም የታገዙ አለመሆንና ከጊዜው ጋር የሚራመድ እንዲሁም ለሌሎች አርአያ መሆን የሚችለ የዘመነ የአሰራር ስርአት በየዘርፉ አለመኖር<br>➢ አንዳንድ ተግባራትን በአግባቡ ለመተግበር የሚያስችሉ የአተገባበር መመሪያዎች የሌሉ መሆናቸው<br>➢ የተጀመሩ የለውጥ ስራዎች የተቆራረጡ መሆናቸው፤ |
| 2 | የአገልግሎት አሰጣጥ | ➢ በተቋሙ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎት አሰጣጦችን ለማዘመን እንዲሁም ወጪ ቆጣቢና የተቀላጠፉ እንዲሆኑ ማድረግ ስራ መጀመሩ፣<br>➢ በክልላዊ ዳታ ማዕከሉ የሲስተምና ድረ ገጽ ሆስቲንግ እና ባክ አፕ አገልግሎት መጀመሩ፣ | ➢ አገልግሎት አሰጣጡ በተቀመጠው በስታንዳርድ መሰረት የሚሰጡ አለመሆናቸው<br>➢ ለሚሰጡ አገልግሎቶች ቅድመ ሁኔታዎችን አን ላይን የማሳወቅ ስርዓት አለመኖርና አገልግሎት አሰጣጡ በራሱ አውቶሜትድ አለመሆናቸው፤<br>➢ የተገልጋይ ዕርካታ በሚፈለግ ደረጃ አለመለየቱ፣ |

| | | አስቻይ ሁኔታዎች | ፈታኝ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የጥንካሬና ድክመት ማሳያ ዋና ጉዳዮች | ጥንካሬ | ድክመት |
| 3 | የሰው ሃይል | ➢ በአንጻራዊ ደረጃ በሴክተሩ የሰለጠነ የሰው ሃይል መኖሩ፣<br>➢ ለከፍተኛ አይሲቲ ባለሙያዎች አድቫንስድ ስልጠና እንዲወስዱ መደረጉ፣<br>➢ | ➢ በሴክተሩ የባለሙያ መደቦች ያልተሟሉ መሆኑ፣<br>➢ ለፈጻሚው ተመጣጣኝ የሆነ የክፍያና የማበረታቻ ስርዓት ባለመኖሩ የሰው ሃይል ፍልሰት ችግር መኖሩ፣<br>➢ የሳይንስ፣ ቴክ/ፈጠ/ስ/ዘርፍ አንፃር ዓላማ ተኮር ዳይሬክቶሬቶች በሚገባ በሰው ሃይል እና በቁሳቁስ ተደራጅተው ወደ ተግባር ሳይገቡ መቆየታቸው፣ |
| 4 | የአመራር ብቃት | ➢ የተቋሙ አመራር አካላት በተቋሙ ዙሪያ የአመለካከት እና የተግባር አንድነት ይዘው እየተንቀሳቀሱ መሆኑ፣ | ➢ አመራሩ አልፎ አልፎ በደራሽ ስራዎች መጠመድ፣ |
| 5 | ስትራቴጂ | ➢ ቢሮው በወጡ ስትራቴጂዎች መሰረት ለመፈጸም ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣ | ➢ ተገቢ በሆነና በተቀናጀ መልኩ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ጉድለት መኖሩ፣<br>➢ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስራዎቻችንን ከፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጂዎቻችን አፈጻጸም ጋር አስተሳስሮ ከመምራት አንፃር ጉድለት መኖሩ፣ |
| 6 | ፋሲሊቲዎች | ➢ ክልል አቀፍ በሆነ መልኩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መስፋፋቱና የመልካም አስተዳደር ስራዎችን ለማቀላጠፍ በወረዳኔት፣ በስኩልኔትና በማህበረሰብ የመረጃ ማዕከላት ደረጃ መዘርጋቱ፣<br>➢ የስልጠና፣ የጥገናና የቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት መኖሩ፣<br>➢ ኢንኩቤተሮች ማደራጃ ማዕከል መኖሩ፣<br>➢ ኢንኩቤቲዎችን በግብዓት ለማጠናከር ጅምር ስራዎች መኖራቸው፣ | ➢ አገልግሎት ላይ የዋለ የኢኮቴ መሠረተ ልማት የጥራትና የብቃት ችግር ያለው መሆኑ፣<br>➢ በሴክተሩ የታቀዱ ሥራዎችን በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችል የተሟላ ተሽከርካሪ እና ሌሎች ግብዓቶች ያለመኖር፣ |
| 7 | ተቋማዊ ባህል | ➢ ጤናማ የሆነ የስራ ግንኙነትና የቡድን መንፈስ /team spirit/ እየተፈጠረ መሆኑ፣<br>➢ የቢሮዉ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች በሲቪል ሰርቫንቱና በህብረተሰቡ ውስጥ ለማስረጽ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መለመዳቸው፣ | ➢ ተሞክሮን የመቀመርና የማስፋፋት ባህል በሚጠበቀው ደረጃ ያለመሆን፣<br>➢ የተነሳሽነትና ፈጠራ ልምድ አናሳ መሆኑ፣ |
| 8 | ፋይናንስ | ➢ ለሴክተሩ የተመደበዉን በጀት የአሰራር ስርዓቱን በመጠበቅ በአግባቡ ስራ ላይ እንዲዉል መደረጉ፣ | ➢ በስትራቴጂያዊ አስተሳሰብና ዕቅድ ላይ የተመሠረተ የበጀት ዕጥረት መኖሩ፣<br>➢ ውጤታማና ቀልጣፋ የግብዓት አቅርቦት ስርዓትን ከመፍጠር አንፃር ዉስንነት መኖሩ፣ |

ለ. ውጫዊ ሁኔታ ትንተና

| | | አስቻይ ሁነታዎች | ፈታኝ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የመመዘኛ መስፈርት | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
| 1 | ፖቲካዊ /ህጋዊ/ | ➢ ያልተማከለ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋቱ፣<br>➢ የማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መኖራቸው፣<br>➢ በመንግስት ለሪፎርም ሥራዎች ትኩረት መስጠቱ፣ | ➢ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት መኖሩ፣<br>➢ አገራዊ እና ክልላዊ የጸጥታ ሁኔታ፣ |
| 2 | ኢኮኖሚያዊ | ➢ ለሴክተሩ መደበኛና ካፒታል ሥራዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት በመንግስት መደገፉ መጀመሩ፣<br>➢ የመሰረተ ልማት አገልግሎት እየተስፋፋ መሆኑ፣<br>➢ ምቹ የፋይናንስ ስርዓት መዘርጋቱ፣<br>➢ ተከታታይና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት መኖሩ፣<br>➢ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ልዩ የገበያ ተጠቃሚነት ደንብ መኖር | ➢ በዓለም አቀፍ ገበያ የዋጋ ግሽበት መኖሩ፣<br>➢ በሴክተሩ የታቀዱ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚያስፈልግ መደበኛና ካፒታል በጀት በወቅቱ አለመለቀቅና በተፈለገው መጠን አለመገኘት፣ /ከፍተኛ የሆነ የበጀት እጥረት መኖሩ/ |
| 3 | ማህበራዊ | ➢ በትምህርትና ጤና ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ እና መረጃ ስርዓታቸውን በአይሲቲ ለማስደገፍ ጥረቶች መጀመራቸው፣<br>➢ በማህበራዊ ዘርፎች ላይ ድጋፍ የሚሰጡ ሀገር በቀል እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች መኖራቸው፣<br>➢ ለልማት አጋዥ የሆኑ ባህላዊና ማህበራዊ ዕሴቶችን የሚያጎለብት ሀገራዊ አደረጃጀት፣ አሰራርና መርሃ ግብር መኖር፣<br>➢ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በጋራ የመስራት ዕድል መፈጠሩ፣<br>➢ የተለያዩ አካላት ስለተቋማችን ያላቸው ግንዛቤ እየጨመረ መምጣቱና ከቢሮችን ጋር የመስራት ፍላጎት መጨመሩ፣ | ➢ ኃላ ቀር የሥራ ባህልና አመለካከት በሲቪል ሰርቫንቱና በህብረተሰቡ ውስጥ መታየቱ፣<br>➢ የኤች አይቪ ኤድስ በሽታ መስፋፋት፣ |
| 4 | ቴክኖሎጂ | ➢ የኢኮቴ መሰረተ ልማት በክልሉ እየተስፋፋ መምጣቱ፣<br>➢ በመስኩ የተሰማሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሃገር የግል ተቋማቶች መኖራቸው፣<br>➢ ቴክኖሎጂውን በብቃት ለማልማት የሚችል የሰው ሃይል በገበያ ላይ መገኘት፣<br>➢ የምርት ጥራት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በሀገር ውስጥ መሰጠት መጀመሩ፣ | ➢ ከቴክኖሎጂዎች ፈጣን ዕድገት መለዋወጥ ጋር ተጣጥሞ አለመሄድ፣<br>➢ የሳይበር ጥቃት እየጨመረ መምጣቱ፣<br>➢ ቴክኖሎጂውን አስታከው የሚመጡ ጎጂ ባህሎች መኖራቸዉ፣ |

| | | አስቻይ ሁነታዎች | ፈታኝ ሁኔታዎች |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የመመዘኛ መስፈርት | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋቶች |
| | | ➢ መንግስት ቴክኖሎጂውን እስከታችኛው የአስተዳደር እርከንና የህብረተሰብ ክፍል ለማዳረስና ለማስፋፋት ፍላጎት መኖሩ፣ | |
| 5 | አካባቢያዊ | ➢ ሴክተሩ በክልሉ መቀመጫ ሰፊ የመንግስት፣ መአድ መስሪያ ቤቶችና ከፍተኛ የትም/ተቋማት ባሉበት መኖሩ፣<br>➢ ለፌዴራል መንግስት ማዕከል ቅርበት ላይ የሚገኝ መሆኑ፣<br>➢ በአብዛኛው የክልሉ አየር ንብረት ለሥራ ምቹ መሆኑ፣ | ➢ ቢሮው በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ የተወሰኑ ዞኖችና ወረዳዎች መራቁ፣ |

## 1.4 የቢሮው ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማዎችና ዕሴቶች

### 1.4.1 ተልዕኮ

ለክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሳይንስና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስራዎችን ለህብረተሰቡ በአግባቡ በማልማት፣ በመተግበርና በማስፋት ክልላዊ ብሎም አገራዊ የተወዳዳሪነት አቅምና በቴክኖሎጂ የዳበረ የአሰራር ስርዓት መፍጠር ነዉ፡፡

### 1.4.2 ራዕይ

"በ2030 በክልላችን ውጤታማ የሆኑ የሳይንስና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት የመማር፣ የማልማት፤ የመፍጠር፣ የማላመድ እና የመጠቀም አቅም ተገንብቶ ማየት"

### 1.4.3 እሴቶች

- ☞ በጎ ህሊናና ቅን ልቦና፣
- ☞ የስራ ፍቅርና ትጋት፣
- ☞ ያልተገደበ አስተሳሰብና ምናባዊ ጉዞ፣
- ☞ ለለውጥ በጋራ መስራት፤
- ☞ ውጤታችንም ሆነ ውድቀታችን የጋራችን ነው፤
- ☞ ችግር ፈቺነት፤
- ☞ የማይረካ የመማር ጥማት፤
- ☞ ለትውልድ የሚተላለፍ መሠረት፣
- ☞ ቀልጣፋና ውጤታማ አሰራርና ቀጣይነት ያለው መሻሻል፣

### 1.4.4 ተቋማዊ ፍልስፍና

- ☞ ዕውቀት ሀብት ነው
- ☞ ለአዳዲስ ሀሳቦች ዕውቅና እንሰጣለን
- ☞ ትጋት የአዎንታዊ ለውጥ ሀይል ነው
- ☞ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የአዲሱ ትውልድ ቋንቋ ነው
- ☞ ኢኖቬሽንን ማበረታታት ለትውልድ ተስፋን መመገብ ነው
- ☞ የዘመነ ዲጅታል ኢኮኖሚ የዕድገታችን መሰረት ነው

# ደረጃ ሁለት

# ተቋማዊ ስትራቴጂን መወሰን

## 2.1 የሴክተሩ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ዝርዝርና ዳሰሳ

### 2.1.1 ተገልጋዮች /የአገልግሎት ተጠቃሚዎች/

- ☞ የክልሉ ነዋሪ ህዝብ፣
- ☞ የግሉ ሴክተር
- ☞ የክልሉ መንግሥት ሴክተር መ/ቤቶች፣
- ☞ በክልሉ የሚገኙ የትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች፣
- ☞ የጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችና አንቀሳቃሾች፣
- ☞ ተመራማሪዎችና የፈጠራ ባለሙያዎች፣
- ☞ የመንግስት አጋር ድርጅቶች

### 2.1.2 ባለድርሻ አካላት

- ☞ የክልሉ ሴክተር መ/ቤቶች፣
- ☞ የትምህርት ሚኒስቴር፣
- ☞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን፣
- ☞ የኢትዮ ቴሌኮም፣
- ☞ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን፣
- ☞ የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን፣
- ☞ የሚዲያ ተቋማት፣
- ☞ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣
- ☞ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ባለስልጣን፣
- ☞ ብሄራዊ ስነ-ልክ ኢንስቲዩት፣
- ☞ የተስማሚነት ምዘና ኤጀንሲ፣
- ☞ የክልሉ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን፣
- ☞ በክልሉ የሚገኙ የምርምር ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች፣
- ☞ የኢትዮጲያ የመረጃ መረብ ደህንነት፣

## ሀ. የተገልጋዮች ፍላጎት ዳሰሳ

| ተቁ | ተገልጋዮችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት | ሴክተሩ የሚሰጠው አገልግሎት | የደንበኛው ፍላጎት መግለጫ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አገልግሎቱ ለምን ዓላማ ይፈለጋል | ጥራት | ወቅታዊነት | የአገልግሎት ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የሴክተሩ ገፅታ |
| ተገልጋይ | | | | | | | | |
| 1 | የክልሉ ነዋሪ ህዝብ | ➢ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍናና ዉጤታማነትን የሚያሰፍኑ አሰራሮችን መዘርጋት | ➢ ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት | በስታንዳርድ መሰረት | ፈጣንና ቀልጣፋ | ------ | አሳታፊ | መልካም ተምሳሌት |
| | | ➢ የተገልጋይ የአሰራር ሥርዓት | ➢ ህዝቡ ባለቤት እንዲሆን | በተቀመጠ ስታንዳርድ መሰረት | ባስፈለገ ጊዜ | ------ | አሳታፊ | መልካም ተምሳሌት` |
| | | ➢ የማህበረሰብ መረጃ ማእከል | ➢ ለፈጣን የመረጃ ልውውጥ ➢ ከቴክኖሎጂ ጋር ማስተዋወቅና ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ | በተቀመጠ ስታንዳርድ መሰረት | ፈጣንና ቀልጣፋ | ------ | የጋራ | መልካም ስም |
| | | ➢ በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ ስልጠና | ➢ በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ለመጨበጥ | በተቀመጠ ስታንዳርድ መሰረት | እንዳስፈላጊነቱ | ----- | አሳታፊ | መልካም ተምሳሌት |
| | | ➢ ችግር ፈቺ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ውጤቶች ማሸጋገር | ➢ ሁለንተናዊ የአኗኗር ለውጥ እንዲመጣ | በተቀመጠ ስታንዳርድ መሰረት | እንዳስፈላጊነቱ | ----- | አሳታፊ | መልካም ተምሳሌት |
| | | ➢ የጥራት ደረጃዎችና ተስማሚነት ምዘና እና ጨረራ ኢንስፔክሽን ማድረግ | ➢ ጥራቱ በተበቀ ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚነት እንዲጨምር | በተቀመጠ ስታንዳርድ መሰረት | እንዳስፈላጊነቱ | ----- | አሳታፊ | መልካም ተምሳሌት |
| 2 | የግሉ ሴክተር | ➢ አዳዲስ አሰራሮችን ማስተዋወቅና አፈጻጸሙን መከታተልና መደገፍ | ➢ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለማድረግ | በተቀመጠ ስታንዳርድ መሰረት | አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ | ምክንያታዊ | በጋራ መግባባት ላይ የተመሰረተ | መልካም ተምሳሌት |

| ተቁ | ተገልጋዩችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት | ሴክተሩ የሚሰጠው አገልግሎት | የደንበኛው ፍላጎት መግለጫ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አገልግሎቱ ለምን ዓላማ ይፈለጋል | ጥራት | ወቅታዊነት | የአገልግሎት ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የሴክተሩ ገፅታ |
| | | ➢ ተገቢዉን መረጃ መስጠት | ➢ ለዉሳኔ አሰጣጥ፣<br>➢ አገልግሎትን ለማሻሻል፣<br>➢ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት፣<br>➢ የቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ስራዎችን ለመደገፍ፣ | ትክክለኛ | በተጠየቀ ጊዜ | | በመተማመን ላይ ተመሰረተ | ተዓማኒነት አጋርነት |
| | | ➢ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን መስራት፣ መደገፍና መከታተል | ➢ ዘመናዊ ቴክኖሎጂበመጠቀም ቢዝነሳቸዉን ለማስፋፋት | በተቀመጠ የአገልግሎት ስታንዳርድ | አስፈላጊ በሆነ ጊዜ | | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | ደጋፊነት |
| | | ➢ በየደረጃው የሚገኘውን አመራርና ባለሞያ ብቃት ማሳደግ | ➢ የማስፈጸም አቅምን ለመገንባት<br>➢ ተልዕኮን ለማሳካት | የማስፈጸም ብቃት መሻሻሉ | አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ | | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ ትምህርትና ስልጠና | ➢ ምርታማነትን ለመጨመርና አገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማሻሻል | በተቀመጠ ስታንዳርድ | ጥያቄው እንደቀረበ | ምክንያታዊ | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ የውጤት ተኮር ስርዓት | ➢ ስትራቴጂን ለመተግበር | የአፈጻጸም ብቃት መሻሻል | አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ | -------- | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | ሴክተር መ/ቤቶች | ➢ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ትግበራ | ➢ ቀልጣፋ አገልጎሎት ለመስጠት | በአገልግሎት አሰጣጥ ዕርካታ | እንደ አስፈላጊነቱ | ------- | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ ጥናትና ምክር | ➢ የማስፈጸም አቅም ክፍተቶችን በመለየት መፍትሄ ለማፈላለግ | በአፈጻጸም ላይ የመጣ ለውጥ | እንደ አስፈላጊነቱ | ምክንያታዊ | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| 3 | | ➢ ዘመናዊ የኢኮቴ መሳርያዎችና የቴክኖሎጂ ስራዎች | ➢ አገልግሎት ለማቀላጠፍ<br>➢ ለቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ | በተቀመጠ ስታንዳርድ | እንደ አስፈላጊነቱ | | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |

| ተቁ | ተገልጋዩችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት | ሴክተሩ የሚሰጠው አገልግሎት | የደንበኛው ፍላጎት መግለጫ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አገልግሎቱ ለምን ዓላማ ይፈለጋል | ጥራት | ወቅታዊነት | የአገልግሎት ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የሴክተሩ ገፅታ |
| | | ➢ ዳታቤዝ፣የድረ ገጽ፣የሶፍትዌርና የኮሚኒኬሽን ስርዓት መዘርጋት | ➢ አገልግሎት ለማቀላጠፍ<br>➢ ለቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ<br>➢ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርአት ለመዘርጋት | ተጠቃሚነት ተደራሽነት | እንደ አስፈላጊነቱ | | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ ምርጥ ተሞክሮ<br>➢ መቀመርና ቴክኖሎጂን የማላመድ ስርዓት | ➢ አዳዲስና የተሻሻለ አሰራርን በመቅሰም በአነስተኛ ወጪና ጊዜ ለመተግበር | በሚያመጣው ፈጣን ለውጥ | እንደ አስፈላጊነቱ | ---- | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| 4 | ትምህርት ቤቶች | ➢ የሳይንስ ክበባት ማቋቋም | ➢ የተማሪዎችን የሳይንስ ዝንባሌ ለማሳደግ | በሚያመጣው ፈጣን ለውጥ | እንደ አስፈላጊነቱ | ---- | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| 5 | ተመራማሪዎችና የፈጠራ ባለሙያዎች | ➢ ለምርምርና ፈጠራ ስራዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠር<br>➢ በተለያዩ መስፈርቶች በመመልመል ማበረታታትና መሸለም | ➢ የህብረተሰቡን ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምርና ፈጠራ ስራዎችን ለማሳደግ | በተቀመጠ ስታንዳርድ | እንደ አስፈላጊነቱ | | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| 6 | በየደረጃው የሚገኙ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተማሪዎች | ➢ ለሳይንስና ቴክኖሎጂዕውቀትና ክህሎት ምቹ ሁኔታ መፍጠር | ➢ በቀጣይ ተማሪዎች የህብረተሰቡን ችግር የሚፈታ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲያክሩ | በተቀመጠ ስታንዳርድ | እንደ አስፈላጊነቱ | | በመደጋገፍ ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |

## ለ. የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ዳሰሳ

| ተቁ | ተገልጋዩ ጉዳዩ ዓይነት | ሴክተሩ የሚሰጠው አገልግሎት | የደንበኛው ፍላጎት መግለጫ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አገልግሎቱ/ምርቱ ለምን ዓላማ ይፈለጋል | ጥራት | ወቅታዊነት | የአገልግሎት ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የሴክተሩ ገፅታ |
| ባለ ድርሻ አካላት | | | | | | | | |
| 1 | የክልሉ መንግሥት | ➢ በየደረጃው የሚገኘውን አመራር ብቃት ማሳደግ | ➢ የማስፈጸም አቅምን<br>➢ ተልዕኮን ለማሳካት | ➢ የመወሰን ብቃት መሻሻሉ<br>➢ ራዕይ ማስፈጸም መቻሉ | አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ | ምክንያታዊ | ተልኮን በማሳካት ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ የኢኮቴ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች ማስተግበር | ➢ የማስፈጸም አቅም ለማጎልበትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና | ➢ የመርሆቹ መተግበር<br>➢ የአፈጻጸም ብቃት ማደጉ | ዘወትር | | ተልኮን በማሳካት ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ የኢኮቴ እና የሳይንስናቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትና አገልግሎት | ➢ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ | ➢ በተቀመጠ ስታንዳርድ | በተፈለገ ጊዜ | | ተልኮን በማሳካት ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ መረጃ አገልግሎት | ➢ ለዉሳኔ አሰጣጥ<br>➢ አገልግሎትን ለማሻሻል<br>➢ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት | ➢ ስምምነት በተደረሰበት ስታንዳርድ | በተጠየቀ ጊዜ | | ተልኮን በማሳካት ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ ጥናትና ምርምር | ➢ የማስፈጸም አቅም ክፍተቶችን በመለየት መፍትሄ ለማፈላለግ | ➢ በአፈጻጸም ላይ የመጣ ለውጥ | እንደ አስፈላጊነቱ | ምክንያታዊ | ተልኮን በማሳካት ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| | | ➢ | ➢ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ድክመትና ስኬት ለመለየት<br>➢ በክፍተቶች ላይ እርምት ለማድረግ | ➢ ለትክክለኛ ውሳኔ የሚረዳ | በተፈለገ ጊዜ | ------- | ተልኮን በማሳካት ላይ የተመሰረተ | አጋርነት |
| 2 | የትምህርት ሚኒስቴር | ➢ መረጃ ድጋፍና ቅንጅታዊ አሰራር | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ለማዘጋጀት | | በተፈለገ ጊዜ | | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| | የጤና ሚኒስቴር | ➢ መረጃ ድጋፍና ቅንጅታዊ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ ፖሊሲዎችና | | በተፈለገ ጊዜ | | በትብብርና የጋራ | አጋርነት |

| ተቁ | ተገልጋዩ ጉዳዩ ዓይነት | ሴክተሩ የሚሰጠው አገልግሎት | የደንበኛው ፍላጎት መግለጫ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አገልግሎቱ/ምርቱ ለምን ዓላማ ይፈለጋል | ጥራት | ወቅታዊነት | የአገልግሎት ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የሴክተሩ ገፅታ |
| | | አሰራር | መመሪያዎች ለማዘጋጀት | | | | መግባባት | |
| 3 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን | ➢ መረጃ፣ ድጋፍና ቅንጅታዊ አሰራር | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ | | በተፈለገ ጊዜ | | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 4 | የኢትዮ ቴሌኮም | ➢ ቅንጅታዊ አሰራርና መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይን ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ---- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 5 | የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኤጀንሲ | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 6 | የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 7 | የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 8 | ብሔራዊ የአዕምሯዊ ንብረትጥበቃ ጽ/ቤት | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 9 | የተስማሚነት ምዘና | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |

| ተቁ | ተገልጋዩ ጉዳዩ ዓይነት | ሴክተሩ የሚሰጠው አገልግሎት | የደንበኛው ፍላጎት መግለጫ | | | | ደንበኛው የሚጠብቀው | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | አገልግሎቱ/ምርቱ ለምን ዓላማ ይፈለጋል | ጥራት | ወቅታዊነት | የአገልግሎት ዋጋ | የግንኙነት ሁኔታ | የሴክተሩ ገፅታ |
| 10 | የአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ቁጥጥር ባለስልጣን | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| | የክልሉ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 11 | በክልሉ የሚገኙ የምርምር ተቋማት | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት | ➢ የትብብርና ድጋፍ አሰራር | ➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 12 | የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር | ➢ ቴክኒካዊ ድጋፍ<br>➢ ቅንጅታዊ አሰራር<br>➢ መረጃ | ➢ ለውሳኔ አሰጣጥ<br>➢ የጋራ ራዕይ ለማሳካት | ➢ በተቀመጠ የጋራ መግባቢያ መሰረት | እንደአስፈላጊነቱ | ----- | በትብብርና የጋራ መግባባት | አጋርነት |
| 13 | ሚዲያ | ➢ መረጃ | ➢ ለህዝቡ ወቅታዊ መረጃ ተደራሽ ለማድረግ | ➢ ተዓማኒነት<br>➢ ወቅታዊነት | በተጠየቀ ጊዜ | --- | በህግ አግባብ | አጋርነት |

## 2.2 የተቋም ስትራቴጂያዊ ትኩረት መስክና ስትራቴጂያዊ ውጤቶችን መለየት

| | የትኩረት መስክ | | ስትራቴጂያዊ ውጤት | የትኩረት መስክ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የትኩረት መስክ 1፡ | የሳይንስ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ እና ዘርፈ ብዙ ትብብሮችን ማጠናከር | የህብረተሰብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተገነባ የልማት አቅምና የምርትና ምርታማነት ስርዓት | በዚህ የትኩረት መስክ የሳይንስ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ፍላጎቶችን እንደ ክልል በመለየትና የማቴሪያል፣ የፋይናንስ እና ቴክኒካል እገዛዎችን ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ክልላዊና ሀገራዊ ትስስርና ትብብር የሚፈጠር ከመሆኑም በላይ በሴክተሩ የሚከናወኑ ስራዎች ከየት ጀምረው ወዴት እንደሚሄዱ የሚያስረዳንና ምን አይነት እገዛዎች እንድሚያስፈልጉንና በምን ሁኔታዎች ላይ እንዳለን የሚያሳይ አሰራር የሚኖር ሲሆን የትስስርና የትብብር ውጤት የሆኑ ፋይናንሻል፣ ማቴሪያላዊ እና ቴክኒካዊ እገዛዎች በሙሉ ወደ ተጠቃሚዎች በማድረስ የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማርካት ይሰራል፡፡<br>**በዚህ የትኩረት መስክ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት፡-**<br>➢ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ስራዎች የሀገራዊና አለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችና የቴክኖሎጂ እድገት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የአቅም ግንባታ ፍላጎት ዳሰሳ ይካሄዳል፤<br>➢ የፕሮጀክት ሃሳቦችን መፍጠርና መቅረጽ ሳይሰለች እንዲሰራ ይደረጋል፤<br>➢ ህዝቡን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ግንዛቤ የማሳደግ ስራዎች ይሰራሉ፤<br>➢ ከድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር አዳዲስ ትስስር እና ትብብር ይፈጠራል ነባር ትስስሮች ይጠናከራሉ፤<br>➢ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሙያ ማህበራት እንዲኖሩና እንዲጠናከሩ ድጋፍ በማድረግ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት የላቀ ድርሻ እንዲኖራቸው ይሰራል፤<br>➢ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተግባራትን የሚያቀላጥፉ ተቋማት እንዲቋቋሙ ይደረጋል<br>➢ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተግባራትን የሚያቀላጥፉ የአሰራር ስረዓት ይዘረጋል የህግ ማዕቀፍ የዘጋጃል<br>➢ ለሴክተሩ ባለሙያዎች ረዥም እና አጫጭር ስልጠናዎችን ማመቻቸት፣<br>➢ የኢኮቴ መሣሪያዎች አያያዝና አወጋገድ ህጋዊ ማዕቀፍ መፍጠርና ማስተግበር<br>➢ ለአእምሯዊ ንብረትና ለፈጠራ ስራ ዉጤቶች ህጋዊ ጥበቃና ዕዉቅና ይሰጣል፡፡<br>➢ ክልላዊ የሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤግዝቢሽን፣ የውይይትና የምክክር መድረኮች እንዲሁም የየሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሳምንት ማክበር፣<br>➢ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የአካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች በአምሯዊ ንብረትና ፈጠራ ስራዎች ያላቸው ተሳትፎና ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስርአት ይፈጠራል፤<br>➢ በኢኮቴ ዘርፍ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች ፍቃድና ብቃት ማረጋገጫ ስርአት ውስጥ የሚገቡ |

| | የትኩረት መስክ | | ስትራቴጂያዊ ውጤት | የትኩረት መስክ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | የድርጅቶችን ቁጥር ማሳደግ |
| 2 | **የትኩረት መስክ 2፡** | **የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ** | **የዲጂታል ኢኮኖሚውን ስርአቱን ማሳለጥ የሚያስችል አስተማማኝ ቀልጣፋና ብቁ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ተደራሽነት** | በዚህ የትኩረት መስክ በዲጅታል መሰረታዊ እሳቤዎች የተቃኙ ምርትና አገልግሎቶች ከዚህም በላይ በርካታ ለውጦችን ለማምጣት የሚያስችሉ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ለማህበረሰብ ተደራሽነት በማረጋገጥና የክህሎትና የዕውቀት ሽግግር ስራዎችን በመስራት ለዲጅታል ኢኮኖሚ ስርአት ግንባታ የሚሆኑ መደላድሎች እንዲፈጠሩ በትኩረት ይሰራል ፡፡<br>**የትኩረት መስኩ ያቀፋቸው ዋና ዋና ጉዳዮች**<br>☞ የማ/መ/ማዕከላትን፣ የማ/ሬዲዮ ጣቢያ እና ኮል ሴንተር ማቋቋምና ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣<br>☞ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን የሚያግዝ ቴክኖሎጂ ክህሎት ስልጠና መስጠት፣<br>☞ በክልሉ በገጠር ቀበሌያት የኢኮቴና የቴሌኮም አገልግሎቶችን የሚሰጡ ማዕከላትን ማቋቋምና ሽቦ አልባ ስልችን በቀበሌያቱ አገልግሎቱ ተደራሽ እንዲሆን ይሰራል፡፡<br>☞ ህጋዊ ዕዉቅና የተሰጣቸዉን የፈጠራ ስራዎችን ጥቅም ላይ እንዲዉል የሚያስችል የማስተዋወቅ ስራ በሚዲያ፣ በበራሪ ወረቀት፣ በመረጃ መረብ፣ በኢግዚቢሽንና ባዛር፣ ይሠራል<br>☞ ክልላዊ የመረጃ መረብ ዝርጋታ ማከናወን፣ማሻሻል እና ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፣<br>☞ የኢኮቴ መሣሪያዎች አቅርቦት አገልግሎት ተግባር ማከናወን፤<br>☞ የኢኮቴ መሣሪያዎች ሶፍተዌር እና ሀርድዌር ጥገና እና እድሳት አገልግሎት፣<br>☞ Government Portal መስራት ተግባራዊ ማድረግ (G-Website)፣<br>☞ የተለያዩ ክልላዊ መረጃ ቋት እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡<br>☞ የመረጃ መረብ ዝረጋታ፣ የሶፍትዌር ልማትና የኢኮቴ መሣሪያዎች ስታንዳርድ ስፔስፊኬሽን ዝግጅትና ቁጥጥር ስራ ማከናወን፡፡ |

| | የትኩረት መስክ | | ስትራቴጂያዊ ውጤት | የትኩረት መስክ ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 3 | የትኩረት መስክ 3፡ | የዲጂታል ኢኮኖሚ ስርዓት ግንባታና ሁሉ አቀፍ ተጠቃሚነትን ማሳደግ | ዘመናዊ ቀልጣፋና ውጤታማ የዲጂታል ኢኮኖሚ ስርአት | በዚህ ትኩረት መስክ የዲጂታል ኢኮኖሚ ዝግጁነት ለማሳደግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዝርጋታ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ በአብዛኛው እነዚህ አሰራሮች ሴክተር ተኮር በሆኑ ዳታ ቤዞች፣ ፖርታሎችና ሲስተሞችን በመገንባት የሚደራጁ የአሰራር ስርአቶች ለማጎልበት በተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የሚደገፉ፣ ሳይንስና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን መሰረት በማድረግ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የስራ ዕድል ፈጠራና እና ሀብት የማፍራት ስራዎች በሰፊው ይሰራሉ፡፡<br>**የትኩረት መስኩ በዋናነት የያዛቸው ቁልፍ ተግባራት፣**<br>☞ የቪዲዮ ኮራፍራንሲንግ እና የዳታ ልውውጥ አገልግሎት መስጠት፣<br>☞ የክልሉን የመረጃ ስርዓት ደህንነት ቁጥጥር ማድረግ፣<br>☞ የዳታ ቅጂ (Back up) አገልግሎት፣<br>☞ ውጤታማ የቴክኖሎጂ ኢንተርፕራይዞችን ማፍራት<br>☞ የተለያዩ ሴፍትዌሮች ማልማት፣ ማላመድ፣ ማስተግበርና ድጋፋዊ ክትትል ማድረግ፣<br>☞ የጨረራ አመንጪ መሳሪያዎችን በመለየትና በመከታተል ህብረተሰቡ ካስከፊ ጉዳት ፣ እንዲጠበቅ የማድረግና በአገልግሎት ላይ እየዋሉ ያሉ መሳሪያዎች የካሊብሬሽን ስራ ማከናወናቸዉን የማረጋገጥ ሥራ ይሠራል፤<br>☞ ምርቶችና አገልግሎቶች የጥራት ደረጃቸውን ስለማሟላታቸው ከሚመለከተዉ አከላት ጋር በትብብር በመስራት አግባብ ያለው ሙያዊ አገልግሎት መስጠቱን ያረጋግጣል፣<br>☞ የክልሉ ህብረተሰብ ከባህላዊ መመዘኛዎች ወደ ዘመናዊ አለካክ እንዲለወጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል፡፡<br>☞ በክልሉ የሚገኙ መለስተኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደቱን በኢኮቴ የተደገፈ ከማረግ አኳዋያ የእስኩል ኔት እና የኢለርኒንግ ስርአቶች እንዲተገበሩ የቴክኒክ ድጋፍ ስራዎች ይሰራሉ፡፡<br>☞ የክልሉን ማህበረሰብ ችግሮች መፍታት የሚያስችሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ስራዎች ይሰራሉ |

## 2.3 ስትራቴጂያዊ ዕይታዎች

- ተገልጋይ
- ፋይናንስ
- የውስጥ ስራ ሂደት
- መማማርና ዕድገት

### 2.3.1 ተገልጋይ

- ሴክተሩ በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ተገልጋዮች ማለትም የመንግስት ተቋማትና ሰራተኞች፣ የክልሉ ህብረተሰብና የግሉ ሴክተር አገልግሎት በምን አይነት ቅልጥፍናና ዉጤታማነት እየሰጠ መሆኑንና የህዝብ አመኔታና እርካታ ማስገኘት እንደቻለ የምናረጋግጥበት እይታ ነዉ፡፡

### 2.3.2 የፋይናንስ /በጀት/ ዕይታ

- ፋይናንስ ተቋማት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ዕቅዶቻቸዉን የሚያሳኩበት ዋና ግብዓት ነዉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ዕይታ ስር እንደ ሳኢቴ ሴክተር ስትራቴጂ የሚመራው፣ ወጭ ቆጣቢ፣ ከውጤት ጋር የተሳሰረና የግልጸኝነትና ተጠያቂነት አሰራር የሰፈነበት የፋይናንስ አፈጻጸም ስርዓት መኖሩ የሚታይበት መነጽር ነዉ፡፡

### 2.3.3 የውስጥ አሰራር ዕይታ

- በዚህ ዕይታ ስር ለተገልጋይ እሴት የሚጨምሩ አፈጻጸሞች እርስ በዕርሳቸዉ በመጋገብና በጋራ በመሆን ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኩን ስኬት ለማረጋገጥ መቻሉ የሚታይበት እይታ ነዉ፡፡ በመሆኑም በሴክተሩ ዉስጥ፡
  - ✓ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አፈጻጸም መጎልበቱን፣
  - ✓ የአገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍና መረጋገጡን እና
  - ✓ አሰራሮች መሻሻላቸዉን የምናይበት የዕይታ ነዉ፡፡

### 2.3.4 የመማማርና ዕድገት ዕይታ

ይህ ዕይታ በሴክተሩ ዉስጥ፡-

- ✓ የሰዉ ሃብት አቅም መገንባቱን፣
- ✓ የኢኮቴ መሰረተ ልማት መሟላቱን፣
- ✓ ተቋማዊ ባህልና ሃብት መጎልበቱን፣
- ✓ ምቹ የሆነ የስራ አካባቢ መፈጠሩን የምናይበት እይታ ከመሆኑም በላይ ከላይ የተጠቀሱትን ዕይታዎች ለማሳካት አቅም የሚገነባበት ነዉ፡፡

# ደረጃ ሶስት

# ስትራቴጂያዊ ግቦች

**ስትራቴጂያዊ ግቦች የትኩረት መስክ 1፡- የሳይንስ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ እና ዘርፈ ብዙ ትብብሮችን ማጠናከር**

**ስትራቴጂያዊ ውጤት፡-** የህብረተሰብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የተገነባ የልማት አቅምና የምርትና ምርታማነት ስርዓት

| ዕይታዎች | ግቦች | የግብ መግለጫዎች | |
|---|---|---|---|
| | | የግብ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
| ተገልጋይ | ምቹ የምርምርና የፈጠራ ስራ ምህዳር በመፍጠር የተመራማሪዎችንና የፈጠራ ባለሙያዎችን ውጤታማነት ማሳደግ | በዘርፉ የሚከናወኑ የምርምር ስራዎች እየገጠማቸው ያለውን ችግሮች በመለየት የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና ሌሎችም እንዲፈቱና ጉድለቶቻቸው ተሟልተው የፈጠራ ባለሙያ የሆኑ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ተመራማሪዎችን በመደገፍ ለማህበረሰቡ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ የምርምርና የፈጠራ ውጤቶች በስፋት እንዲፈልቁ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወን፣ | ምቹ የስራ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ውጤታማ ስራዎችን ማከናወን የቻሉ የፈጠራ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች፣ |
| | ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርአት ማረጋገጥ፣ | በሴክተሩ የሚሰጡ ሁሉም አገልግሎቶችን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና የመረጃ ልውውጥ ስርዓቶችን በመዘርጋት ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ መግባባት በመፍጠር ተጠያቂነት የሰፈነበት የአሰራር ስርዓት እንዲፈጠር ማድረግ | ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ የአሰራር ስርዓት |

| ዕይታዎች | ግቦች | የግብ መግለጫዎች | |
|---|---|---|---|
| | | የግብ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
| ፋይናንስ | የበጀት አጠቃቀምን ውጤታማነትን ማሳደግ | ዕቅድንና የወጪ ቁጠባን መሠረት ያደረገ ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም የሚያካትት ነው፣ | ተግባራትን ለማስፈጸም የሚያስችል በቂ በጀት |
| ውስጥ አሰራር | ቀልጣፋና ውጤታማ የአሰራር ስርአት ማረጋገጥ፣ | በሴክተሩ የሚሰጡ ሁሉም አገልግሎቶችን ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና የመረጃ ልውውጥ ስርዓቶችን በመዘርጋት ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ መግባባት በመፍጠር ተጠያቂነት የሰፈነበት የአሰራር ስርዓት እንዲፈጠር ማድረግ | ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሐዊ የአሰራር ስርዓት |
| | ብቁና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማትንመፍጠር | በክልሉ የሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን አገልግሎቶችና የምርምር ስራዎችን ለህብረተሰቡ በብቃትና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ተደራሽ የሚያደርጉ ተቋማትን ማቋቋም፤ ማስፋፋትና ማጠናከርን የሚያካትት ነው | በግብዓት የተጠናከሩ ብቁ ቀልጣፋና ውጤታማ ተወዳዳሪነታቸው ያደገ ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት |
| | ውጤታማ የትብብር ስርአትን ማረጋገጥ፣ | ውጤታማ የዩኒቨርሲቲ ኢንደስትሪ ትስስርና ሌሎች ቅንጅታዊ የትብብር ስርዓትን በመፍጠር የሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ስራዎችን ለመስራት፤ ለግለሰቦችና ተቋማት አዲስ የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ መስጠትና ማደስ እንዲሁም መሰል ስራዎች ይከናወናሉ፣ | የተፈጠረ ውጤታማና ጠንካራ ክልላዊ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ትብብር ስርዓት፣ |
| መማማርና ዕድገት | ምቹ የስራ አካባቢን መፍጠርና የሰው ሃብት ውጤታማነትን ማሳደግ | አጠቃላይ የሰራተኞችን የአቅም ግንባታ ስራዎች ማከናወንና ምቹ የሆነ የስራ አካባቢን በመፍጠር የሰራተኞች የስራ | የተፈጠረ ምቹ የስራ አካባቢ እና ያደገ የሰራተኞች ውጤታማነት |

| ዕይታዎች | ግቦች | የግብ መግለጫዎች | |
|---|---|---|---|
| | | የግብ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
| | | ተነሳሽነት የሚጨምርና ውጤታማነታቸውን የሚያሳድግ ስራ የሚከናወንበት ግብ ነው፡፡ | |

**የትኩረት መስክ** 2 የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ተጠቃሚነትን ማሳደግ

**ስትራቴጂያዊ ውጤት**:- የዲጂታል ኢኮኖሚ ስርአቱን ማሳለጥ የሚያስችል አስተማማኝ፣ ቀልጣፋና ብቁ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ተደራሽነት

| ዕይታዎች | ግቦች | የግብ መግለጫዎች (Objective commentary) | |
|---|---|---|---|
| | | የግብ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
| ተገልጋይ | የዲጂታል ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችና አቅርቦቶች አጠቃቀምን ማሳደግ፣ | ለዲጂታል ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚያስችሉ ጥራትና አስተማማኝነት ያላቸውን የቴክኖሎጂ ቁሳቁሶች አቅርቦት እንዲኖር ማስቻል፣ | ያደገ ጥራት ያለው የዲጂታል ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች አጠቃቀም፣ |
| | የማህበረሰብ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | የማህበረሰቡን የዲጂታል አገልግሎት ግንዛቤና ክህሎትን በማሳደግ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ተገቢ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ማዕከላትን ማቋቋምና ማጠናከር፤ ስራዎች የሚሰሩበት ግብ ነው፡፡ | የዲጂታል አገልግሎት ክህሎትና ግንዛቤው ያገኘና ተጠቃሚ የሆነ ማህበረሰብ |
| | የዲጂታል አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ቁጥር ማሳደግ | የዲጂታል አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማት በማቋቋም ሌሎች የማደራጀትና የማስፋፋት ስራዎች የሚሰሩበት ግብ ነው፡፡ | ብቁና ቀልጣፋ የዲጂታል አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተቋማት |
| ፋይናንስ | የበጀት አጠቃቀምን ውጤታማነትን ማሳደግ | ዕቅድንና የወጪ ቁጠባን መሠረት ያደረገ ውጤታማ የበጀት አጠቃቀም የሚያካትት ነው፣ | ተግባራትን ለማስፈጸም የሚያስችል በቂ በጀት |

| ዕይታዎች | ግቦች | የግብ መግለጫዎች (Objective commentary) | |
|---|---|---|---|
| | | የግብ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቅ ውጤት |
| ውስጥ አሰራር | ውጤታማ የሆኑ የቴክኖሎጂ ሀርድዌሮችና ሶፍትዌሮችን ተደራሽነት ማሳደግ | በክልሉ ተቋማት ብቁና ውጤታማ የቴክኖሎጂ ሃርድዌሮችና ሶፍቴዌሮችን ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በመለየት አቅርቦቱን ተደራሽ በማድረግ የአገልግሎት ቀጣይነት እንዲኖር የሚያስችሉ ስራዎች የሚከናወንበት ግብ ነው | ብቁና ውጤታ ማ የሆኑ የቴክኖሎጂ ሃርድዌሮችና ሶፍትዌሮችን ተደራሽነት ማረጋገጥ |
